# የቶሮንቶው ሕዝባዊ ስብሰባ በታላቅ ስኬት ተጠናቀቀ

ካናዳ ውስጥ ቶሮንቶ ከተማ ላይ ጁላይ 16 ቀን 2011 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) እና የሌሎች አንድነት ሃይሎች ደጋፊዎች ተጠርቶ የነበረው ሕዝባዊ ስብሰባ በታላቅ ውጤት ተጠናቁዋል። የዚህ ስብሰባ አዘጋጆች በመድረክ ተናጋሪነት ያቀረቡዋቸው እንግዶች አቶ ፋሲካ በለጠ (ከኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ)፡ ወ/ሮ ገነት ግርማ (ከኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሴቶች ድርጅት)፡ አቶ አሊ ሰኢድ (ከኢትዮጵያ ፖለቲካ እሥረኞች አንድነት ኮሚቴ)።ዶ/ር አበበ ወርቁ (በግላቸው ከቶሮንቶ አካባቢ ኑዋሪ ኢትዮጵያዊያን) እና ከኢሕአፓ የወጣት ክንፍ ወጣት ታዘበው አሰፋና ወጣት ደሪባ ታቱ ነበሩ።



*የክብር እንግዶች - ከቀኝ ወደ ግራ፡ አቶ ፋሲካ በለጠ፣ ወ/ሮ ገነት ግርማ፤ አቶ ሙሉቀን ሙጩ (አስተናባሪ)፣ አቶ አሊ ሰዒድ፣ ዶ/ር አበበ ውርቁ፣ ወጣት ታዘበው አሰፋ እና ወጣት ደሪባ ታቱ*

የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስርኞች አንድነት ኮሚቲን ወክለው የተገኙት አቶ አሊ ሁሲን ሰዒድ፣ ዋና መሥሪያ ቢቱ በጀርመን ሀገር በርሊን ውስጥ የሆነው ድርጅታቸው ከተመሰረተ ከ1995 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ጀምሮ ያደረገውን እንቅስቃሲና ያከናወናቸውን ተግባሮች ዘርዘር አድርገው አቅርበዋል። ከዋና መሥሪያ ቢቱ በሚሰጥ መመሪያ መሰረት በተለያዩ የዓለም አካባቢዎቸ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትና የሥራ እንቅስቃሲዎቸ ያሉት ሲሆን ከዚህ አኩዋያ እሳቸውም በካናዳ ውስጥ ይኸውን የሰብአዊ መብት ተቆርቁዋሪ ድርጅት በመወከል ብዙ አመርቂ በጎ ተግባሮችን እንዳከናወኑ ዘርዝረዋል። ከእንቅስቃሴዎቻቸው መካከል ብዛት ያላቸው ስደተኛ ኢትዮጵያዊያንን እንደረዱና በቋዋሚ ኑዋሪነት ወደ ካናዳ መጠውም ኑሮአቸውን መልሰው እንዲመሩ በማድረግ ከፍተኛ ሚና እንደተጫዎቱ ከመግለጣቸው በተጨማሪ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደርሱ የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰት በጾታ፤ በሃይማኖት፤ በዘርና በፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ሳያደርጉ በግንባር ቀደምትነት የታገሉ መሆኑን ተግባራዊ መረጃዎችን እየጠቀሱ አስረድተዋል። በካናዳ ውስጥ የሚገኘው የድርጅታቸው፣ ማለትም የኢትዮጳያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቲ (Solidarity committee of Ethiopian Political prisoners-SOCEPP) ቅርንጫፍ በተለያዩ ጊዚዎቸ በካናዳ ውስጥ ላሳየው መልካም ምሳሊያዊ ተግባር ከፍትኛ አደናቆት ከማትረፋና በሰብአዊ መብቶቸ ጉዳይ ስምሪት ላይ ከተለያዩ መሰል መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ተቋዋሞች ጋር እኩል ተሳትፎ ከማድረጉ በላይ፣ በካናዳ ሰብአዊ መብቶቸ ኮሚሽን (Canada Human Rights Commission)፤ በማኒቶባ ሰብአዊ መብቶቸ ኮሚሽን (Manitoba Human Rights Commission) እና በሰብአዊ

*መብቶች ነጻነት ማህበር (Human Rights Liberty Association) አመካይነት የተዘጋጀው የ2009 የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ቃልኪዳን ሽልማት (Human Rights Commitment Award) ባለቤት ለመሆን መብቃቱን አረጋግጠዋል።*



*ከቀኑ ስብሰባ ተካፋዮች በከፊል*

*መሠረቴና የእምነት ፈርጄ ኢሕአፓዊነት ነው የሚሉት አቶ አሊ ሰዒድ፤ ፖለቲካዊ እምነትንና አቋዋምን በምንም መንገድና ሁኔታ ሳይጣረር ሰፊ ለሆነ ሕዝባዊና ሀገራዊ ተልዕኮ መሰለፍ ይቻላል፣ በተግባርም እያረጋገጥነው ነው ይላሉ። ለፍትህ ርትዕ መጋደልን፡ ለእኩልነት፣ ለዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች በጽናት የመዋደቅን ኢሕአፓዊ ባህርይ ወርሶ ከፖለቲካ ሥልጣን ትግል ባሻገር ለአጠቃላዩ የሰው ልጆች የጋራ ፍላጎትና ደህንነት ድንበር፡ ዘር፣ ሃይማኖትና የግል ፖለቲካዊ አመለካከት ሳይከልል ከማንኛውም ቅን አሳቢ የህብረተሰብ ክፍልና ስብስብ ጋር በግልና በጋራ መሥራት ይቻላል፣ ተችሉዋልም ብለዋል። ድርጅታቸው በሀገር ውስጥ የአምባገነኑ የመለስ ዜናዊ መንግሥት አካልና አይነታ የነበረው ስዬ አብርሃ ኢፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ ለእሥር ሲዳረግ የግፍ እሥረኛው ፍትህ እንዲያገኝ መታገሉን፤ ለእነ አቶ አበራ የማነ አብ ያላቋዋረጠ ድምጽ በመሆን፤ እነ ወ/ሮ ብርቱካን ሚደቅሳ በቂም በቀል ግፍ ተፈጽሞባቸው በእሥር ሲማቅቁ ለፍትሃዊ መብታቸው መጠበቅ ሳያሰልስ መታገሉን፣ ለምሳሌ ያህል በቅርቡ በወሎ ዩኒቨርሲቲ ከኮምቦልቻ ካምፓስ በእምነታቸው ምክንያት ታፍነው የተወሰዱ ስድስት የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች ላይ የተወሰደውን ፍትሃዊነት የጎደለው እርምጃ አጥብቆ በመቃወምና ወደፊትም የሰው ዘርን ሊያጠፉና የሰላማዊ ሕዝብን ኑሮ ሊያውክ በማይችል ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ የማነኛውንም ሃይማኖቶች መብት የሚያስጠብቅ መሆኑን፤ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ እሥረኞች አንድነት ኮሚቴ ጎን የሚቆሙ በርካታ ዓለም አቀፍ የዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብት ታጋዮችን በአጋርነት ማፍራቱንና ሌሎችንም ብዛት ያላቸው የትግላቸው ውጤት የሆኑ ተግባሮችን ጠቅሰዋል። በአንድ ተሰብሳቢዎችን ለፈገግታ በጋበዘ አባባላቸውም መለስ ዜናዊ ቀኑ ደርሶ አለአግባብ ኢፍትሃዊ በሆነና ሰብአዊነት በጎደለው ሁኔታ ቢንገላታ ለመብቱ እንቆማለን ብለዋል። ብዙዎቹ ተሳታፊዎች ተናጋሪው ቃላቸውን እንደሚጠቁ ግንዛቤ ቢወሰዱም የትንቢታቸው ቀን መድረሻው “መቸ ይሆን!?” በሚለው ግን ሳያረምሙ እንደማይቀር ይገመታል።*

*ሁለተኛው ተናጋሪ ዶ/ር አበበ ወርቁ ነበሩ። እኒህ ምሁር ስለሰው ልጆች ሰናዬ ሕይወት (Wellbeing) አስመልክቶ ዓለም አቀፍ ጥናቶችንና መስፈርቶቸን መሰረት አድርገው ከሀገራችን ከኢትዮጰያ ተጨባጭ ሁኒታ ጋር አነጣጥረው ሰፊ ምሁራዊ ገለጣዎችን ድርገዋል። ዶ/ር ወርቁ ባደረጉት ሰፋ ያለ ገለጻ የተሙዋላ እድገት ሲባል ሂሳባዊ የቁጥር ስሊት ሳይሆን፤ በሚሠሩ ህነጻዎቸና መንገዶቸ ቁጥር የሚለካ ሳይሆን፤ ወይም ደግሞ በደሞዝ ጨማሪና በገቢ መጨመር ብቻ የሚመዘን ሳይሆን የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶችን፤ የሰው ልጆችን ክብርና ነጻነት የግድ ያካተተ ሲሆን ነው በማለት በአጽንኦት ገልጸዋል።*



ወ/ሮ ገነት ግርማ በእራት ግብዣው ላይ ከተገኙ ካናዳዊያን እንግዶች ጋር ሲወያዩ

ከዚህ አኩዋያም ባሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ ውስጥ ይታያል የሚባልው እድገት ከሚሰሩትና ከሚታዩት ታህታይ መዋቅራዊ እንቅስቃሲዎች አኩዋያ በከፊል እወነት ቢሆንም የተሙዋላ እድገት ጅማሪዎች ናችው ሊባሉ ግን ከቶውን አይችሉም ብለዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ የዲሞክራያዊና ሰብአዊ መብቶች መጣስ እስካለ ጊዚ ድረስ (መኖሩ እርግጥ ነው)፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱና ነጻነቱ እስካልተጠበቀ ጊዚ ድረስ፣ በዓለም አቀፍ የእድገት መመዘኛዎች ሀገራችን እንዲት ኒጀር ከተባለች አፍሪቃዊት ሀገር በልጣ ከመግኘቱዋ በቀር የመጨረሻዋ ድሃ ሀገር ተብላ ስትመዘገብ ኢትዮጵያ ውስጥ እድገት አለ ማለቱ እጅግ ከባድ መሆኑን አብራርተዋል። ከሀገር ደርሰው የሚመለሱ አንዳንድ ወገኖች በመሰራት ላይ ያለውን ህንጻና መንገድ ብቻ ተመልክተው፤ በተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል የሚዘዋወርን የገንዘብና የፋይናንስ አቅም አስተውለው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እድገት ተጀምሩዋል ማለታቸው ስህተት ላይ የሚጥላቸው መሆኑንም አክለው አብራርተዋል። ለአንድ ሀገር ሕዝብ እድገት ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶቹ፤ ክብሩና ነጻነቱ የማይነጣጠሉ እሴቶቹ ናቸው በማለት በሀገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ወቅታዊ ሁኒታ አሰደማሚ የሆነ ምሁራዊ ትንተናቸውን በማቅረባቸው ካዘጋጆችና ከታዛቢዎቸ ዘንድ ይበል አሰኝቶላቸዋል።

ቀጣይዋ ተናጋሪ ወ/ሮ ገነትተ ግርማ ነበሩ። ወ/ሮ ገነት በስብሰባው ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሴቶች ድርጅትን ወክለው እንደመሆኑ ሁሉ በሀገር ቢትና በውጭ ሀገሮቸ ባሉ እህቶቻችንና እናቶቻቸን በጾታቸው ምክንያት እየደረሰባቸው ያለውን አስቃቂ በደልና ጭቆና በዝርዝር አቅርበዋል። በአሁኑ ወቅት በስደት በአረብ ሀገሮቸና በሌሎቸ የዓለም አካባቢዎቸ የሚገኙ እህቶቸቸን እየደረሰባቸው ያለውን ዘግናኝ ሁኔታ ለድርጅታቸው ከደረሰው መረጃና በተግባር ከተነቀሳቀሱባቸው ገጠመኞቸ በመነሳት ለተሰበሳቢዎቸ በጥቃት ስሜት የሚያንገበግብ መልእከቶቸን አስተላልፈዋል። ለበደልና ጉዳት የተዳረጉትን እህቶቻችን ሁኔታና ድርጅታቸው በተቻለ አቅም የኢትዮጵያዊያን እህቶቻችን መብት ለማስጠበቅና ጉዳት የደረሰባቸውን በመንካከብ ደረጃ ያደረገውን ጥረት አብራርተዋል።



አቶ ፋሲካ በለጠ በእራት ግብዣው ላይ ለተገኙ ደጋፊዎችና ተባባሪዎች ምስጋና ሲያቀርቡ

ወ/ሮ ገነት ከዚህ መሰሉ የሲኦል ኑሮ መላቀቅ የሚቻለውና እህቶቻችንና እናቶቻችን እኩል የህብረተሰቡ አካል ሆነው መብታቸውን ሊያስጠብቁ የሚችሉት ተደራጅተው ለመብታቸውና ለነጻነታቸው መታገል ሲችሉ ብቻ ነው ብለዋል። ተደራጅቶ ለተሙዋል አመብት መታገል አማራጭ የሌለውም የሚሉት ወ/ሮ ገነት፤ በዚሁ አላማ መሠረት የተደራጀው የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሴቶች ድርጅት በአሁኑ ወቅት ምህዋሩን በማስፋት በተለያዩ ዓለም አካባቢ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ሴቶችን መብት ከማስጠበቅና ድምጽ ሆኖ ከመጮህ በተጨማሪ ከሌሎች መሰል አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር ትብብርን በመፍጠር፣ በድርጅቱ ስም በተከፈተው ፓልቶክና በራዲዮ ቃለ መጠይቆችን በተለያዩ የሴቶች ጉዳይ ላይ በማድረግ፤ ሰፊ እንቅስቃሴ አድርጉዋል፣ በማድረግ ላይም ይገኛል ብለዋል። ወገን የሆኑ ኢትዮጵያዊያንና የሚመለከታቸው ሁሉ የሲቶቸን መብት በማስጠበቅ እንቅስቃሲ ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ የሚያደርጉት ወ/ሮ ገነት ወንዶቹ ኢትዮጵያዊያን የእህቶቻቸውንና የእናቶቻቸውን፤ የፍቅረኞቻቸውንና የትዳር ጉዋደኞቻቸውን መብት በመጠበቅና በማስጠብቅ ረገድ የሚያደርጉት አስተዋጻኦ የትግሉ አካል ሆኖ መቆጠርና ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ሲሉም አሳሰበዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲን(ኢሕአፓ) ወክለው የተገኙት አቶ ፋሲካ በለጠ በበኩላቸው ባቀረቡት አጠር ያለ ግንዛቤ ስለ የኢሕአፓ ውልደትና ታሪካዊ ሚና፤ ስለኢትዮጵያና አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፤ የህብረትንና ትብብርን ጥያቄ አስመልክቶ ከማብራራታቸውም በላይ ለመሠረታዊ ለውጥና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ምን መደረግ አለበት በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ አጽንኦት ሰጥተው አብራርተዋ።

አቶ ፋሲካ ኢሕአፓ በፖለቲካ ድርጅትነት እንዲመሠረት ያበቃውን ከዛሬ 40 ዓመታት በፊት በንጉሳዊው ሥርዓት ውስጥ የነበረውን ተጨባጭ ሁኔታ አንስተው አንኩዋር አንኩዋር በነበሩት ሕዝባዊ ጥያቄዎች ላይ፤ ማለትም በመሬት ላራሹ ጥያቄ፤ ላልተሸራረፈ የዴሞክራሲያዊና የብሄር/ብሄረሰቦች የእኩልነት መብት መከበር ኢሕአፓ ታግሎ ያታገለበትን አንጸባራቂ ታሪክ አውስተዋል። ፓርቲው በተራዘመ ትግሉ ውስጥ የተነሳ የወደቀባቸውን; ከትግሉ የገበያቸውን ተሞክሮዎችና ያሻሻላቸውን የፕሮግራም ነጥቦች አውስትው ከዚህም አንጻር ገና በ1984 (እ.ኤ.አ) መጀመሪያ ላይ በነጻ መሬቱ በሀገር ውስጥ ባካሄድው 2ኛ ጉባኤው “የላብ አደር አምባገነንነት” የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ እንደሻረ፤ በአኩዋያው “መድብለ ፓርቲ” ማለትም የብዙሃን ፓርትዎችን የፖለቲካ ተሳትፎ እንዳጸደቀ፡ የገበያ ኢኮኖሚን እንደተቀበለ በመዘርዘር ከዋና ዋና የፕሮግራም ማሻሻያዎች መካከል እንደሆኑ ከማስረዳታቸው በተጨማሪ በአሁኑ ሰዓት የኢሕአፓ የፖለቲካ መመሪያ ማህበራዊ ዴሞክራሲ (ሶሻል ዴሞክራሲ) መሆኑንም ገልጸዋል።



ወ/ሮ ገነት ግርማ በቶሮንቶ ታዋቂ ከሆኑ የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች ተቆርቋሪ ዜጎች ጋር

*የኢትዮጵያን ተጨባጭ ፖለቲአክዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖማዊ ሁኔታም አጭርና አመርቂ በሆነ ሁኔታ ዳሰውታል። ኸደም ያሉት ተናጋሪ ዶ/ር አበበ ወርቁ ያዘከሩትን ሳይንሳዊ የዕድገት ትንታኔ በመደገፍና በመንተራስ ኢትዮጵያ ውስጥ፡ይታያል የሚባለው እድገት በአደግኛ ሁኔታ ጥገኛ መሆኑንና በሕዝብ ፈጠራና ተሳትፎ ያልተገነባ፣ በእርዳታና ብድር ላይ የቆመ፤ ለተሙዋላ ቀጣይ ዕድገት መሠረት የሌለው ነው ብለውታል። የወያኔ/ኢሃዴግ መንግሥት እድገት በሚለው ቡዋልቱ የሚያስተጋባው በሀገሪቱ ስም የሚያጋብሰውን ብድር ሳይጨምር ወደ 4 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ከምዕራብ መንግሥታት የሚያገኘውን እርዳታ፤ ከውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ሌሎች ባለጉዳዮች በቀጥታ በህጋዊ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ የሚያስተላልፉትን አንድ ቢሊዮን ዶላርና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ የሚፈሰውን አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር፤ በአጠቃላይ ከውጭ በጊዜያዊነትና ቀጣይነቱ ባልተረጋገጠ ሁኔታ በዓመት ወደ 6.5 ቢሊዮን ዶላር የዘነበለትን እሴት አካቶ መሆኑንና ገና ከመጀመሪው ለሥልጣን ሲበቃም በሀገሪቱ ላይ ተጭኖ የነበረው የውጭ ሀገሮች ብድር እዳ የተሰረዘለት መሆኑንና ይህም የካፒታል ስርጭትና ፍሰት ሀገሪቱን እየገዛና እየናዘዘ ባለው ሥርዓት ቁጥጥር ሥር መዋሉን ጥልቀት ባለው ሁኔታ አስረድተዋል። ከዚህ ጋር አያይዘውም፤ ለንፅጽር ይረዳ ዘንድ ከወያኔ ኢሃአዴግ ሥርዓት በፊት የነበረው የወታደራዊ ሥርዓት በብድር መልክ ከውጭ ያገኝ የነበረው ገንዘብ በዓመት 1.7 ቢሊዮን ዶላር ብቻ እንደነበር ጠቁመዋል። የአሁኖቹ ወደ 6.5 ቢሊዮን በዓመት ከፍ ማለቱን ማስተዋል ሲገባ፣ ይህም የመዕራብ ሀገሮችን ብድርና ከምሥራቅ ሀገሮች የሚለገሳቸውን እርዳታም ይሁን ብድር ሳይጨምር መሆኑን ልብ ይሉዋል። ለምን? ብሎ መጠየቅና ለሕዝባዊ ሥርዓትና ተጠያቂነት ላለው አስተዳደር መታገል ግን የዜጋ ሁሉ ግዴታ መሆኑን አቶ ፋሲካ አስገንዝበው አልፈዋል።*



ከአራት ግብዣ ተሳታፊዎች መካከል

በህብረት ጥያቄ ዙሪያ ኢሕአፓ በአስፈላጊነቱ አምኖ እንደ መርህ እንደሚከተለውና ለስኬታማነቱም ረጅም ትግልና መስዋእትነት እንደከፈለበት አስረድተዋል። ሕዝባችን የተለያየ ጥቅምና ፍላጎት እንዳለው ሁሉ ጥቅሙንና ፍላጎቱን የሚያስጠብቁለት የተለያዩ የእንቅስቃሴ ክፍሎች ይኖሩታል። ሕዝብን በጋራ ለማገልግልና የሀገርን ደህንነት ለመጠበቅ ከነዚህ የተለያዩ ክፍሎች ጋር ማበር፤ መተባበርና ተደማምጦ በጋራ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል ብለዋል። ለዚህም ኢሕአፓ ምንጊዜም ቢሆን የህብረትንና የትብብርን ጥያቄ ወደጎን አያደርገውም ሲሉም አጽንኦት ሰጥተውታል። ዋናው ቁምነገር በሂደት ከገበየነው የህብረት ጥያቄና ተግባራዊ አንቅስቃሴ ተመክሮ ተነስተን ምን አይነት ቀጣይና ዘላቂ ህብረት የሚለው ነው ሲሉም መጣኤውን የህብረትና የትብብር አቅጣጫ አመላክተዋል።

ከአቶ ፋሲካ ንግግር በሁዋላ ቀጣዩን የመነጋገሪያ መድረክ የያዙት ከኢሕአፓ የወጣት ክንፍ (ወክንድ) የተወከሉት ወጣት ታዘበው አሰፋና ወጣት ደሪባ ታቱ ናቸው። ወጣቶቹ ሀተታ አላበዙም፤ የኢሕአፓን የጀግንነት ታሪክ ተረክበናል፤ በቆራጥነት መታገልና ፍጻሜ ማድረስ የእኛ፣ በሞራል፤ በገንዘብና በሃሳብ መደገፍ የእናንተ የቀዳሚ ትውልዶችና የሰፊው ሕዝብ ክፍሎች ነው የሚል መሪ ሃሳብ ከማስተላለፍ በስተቀር።

ወጣት ታዘበው አሰፋ ለኢሕአፓ እውን መሆንና በኢሕአፓ የተመራውን ወጣት ትውልድ ታሪክ በአጭር አስገንዝቦ ያ ትውልድ የከፈለውናን ያስተላለፈውን አኩሪ ቅርስና ኢሕአፓን በጽናት ያስቀጠሉትን ቀደምት ትውልዶች አወድሶ እነሆ አርማችሁን አንስተን ትግል ቀጥለናል ብሉዋል። ከተመሠረተ ገና ጥቂት ዓመቶች የሆኑት ወክንድ በአሁኑ ሰዓት ወጣቱን በሀገር ቤትና በውጭ ሀገሮች እያደራጀ መሆኑን አብስሩዋል። ሳይማር አስተምሮ ለቁም ነገር ላበቃን ሕዝባችን የመታደግ ድርሻችን እንወጣለን ያለው የወክንድ ተወካይ አላማችን እውን እንዲሆን ሁሉም ታግለው ከሚያታግሉና ትግሉን በቁርጠኝነት ከተያያዙት እንቅስቃሴዎች ጎን ይሰለፍ ብሏዋል።

ወጣት ደሪባ ታቱ በበኩሉ ባቀረበው አጠር ያለ ንግግር፤ የሁሉ ነገር ማጠንጠኛ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚደረገው ተጋድሎ ነው ሲል አጠቃሎታል። ለሁላችን መኖሪያና መተዳደሪያ ለምትሆነን ዴሞክራሲያዊት ሀገር ልዩነታችን አቻችለን በጋራ በመታገል ለሁላችን የምትመች ሀገር እንገንባ ሲል አሳስቡዋል። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሁሉንም ተሳትፎ እንደሚሻና ውጤቱም ለሁሉም መሆኑን ለተሳታፊዎች በማስታወስ በአመንበትና በምንፈልገው መንገድ ትብብራችንና ድጋፋችን እንለግስ፤ መስመራቸውና ዓላማቸው ለትግሉ የሚጠቅሙ እንቅስቃሴዎችን ሁሉ

ከመተባበርና ከመደገፍ ወደሁዋል አንበል ከማለቱም በላይ አጼ ምኒልክ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተባብረው እንዴት ለታሪካዊው የአድዋ ድል እንደበቁ ትምህርታዊ ምሳሌያዊነታውን ጠቅሶ አልፏዋል።



በእራት ግብዣው ላይ ከተገኙት መካከል

በመጨረሻም እንግዶች አንድ በአንድ ንግግራቸውን ካጠናቀቁና የጥቂት ደቂቃዎች እረፍት ከተሰጠ ቡዋላ በቀጥታ ወደ ጥያቄና መልስ፤ አስተያየትና ገንቢ የሃሳብ ጥቆማዎች ተገብቶ አመርቂ ውይይት ተካሂዱዋል። ከጊዜ ጥበት አኩዋያ ከቤቱየተነሱት ጥያቀዎችና አስተያየቶች ብዙም ባይሆኑም በአይነታቸውና ባቀራረባቸው ግን ሥርዓት የጠበቁ፡ ሀገራዊና ሕዝባዊ ጉዳዮችን ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ በሳል ነጥቦች ነበሩ።



ውጣት ታዘበው እህቶች ላቀረቡለት ጥያቄ ማብራሪያመልስ ሲሰጥ

እለቱ የተጠናቀቀው ከስብሰባ በሁዋላ በላሊበላ ምግብ ቤት በተዘጋጀ የእራት ግብዣ ሲሆን በዚያም በስብሰባው ላይ የነበሩና በተለያዩ ምክንያቶች የቀኑ የስብሰባ ሰዓት ያመለጣቸው ወገኖች በብዛት መጥተው ተሳትፈዋል፡ ከእንግዶች ጋርም በግልና

በጋራ ተነጋግረዋ። ከኢትዮጵያዊያን ማህበረሰብ አባላት ውጭም ሌሎች ካናዳዊያን ዜጎች በእራቱ ግብዣ ላይ ተገኝተው በመካፈል ከክብር እንግዶች ጋር ተዋውቀዋል፤ ቀጣይ ወዳጅነትንም መሥርተዋል።